# ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21-31/2019 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስራአንድ ቀናት ደረቅ፣ ፀሃያማ እና ነፋሻማዉ የአየር ሁኔታ በአብዛኞዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸዉ ነበር የተስተዋለዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ ምንም እንኳን አንፃራዊ በሆነ መልኩ የመሻሻል ሁኔታ ቢታይበትም፤ በአንዳንድ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ እና የምስራቅ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከሞላ ጎደል ቀጥሎ ተስተዉሏል፡፡ በተጨማሪም የቀኑ ዝቅተኛ ሙቀት በአንዳንድ በተጠቀሱ አካባቢዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴ. በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በባቲ 0.5 እና 2.4፣ በሀረማያ 1.0 እና 2.8፣ በደብረብርሃን -2.0, 1.0 እና 2.0፣ በጅማ 2.4፣ በቢሾፍቱ 2.4 እና 4.6፣ በመሃል ሜዳ 2.0፣ በባሌሮቤ 4.5 እንዲሁም በወገል ጤና 4.8 በዲግሪ ሴ. ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ከነበረዉ ደመና በጉጂ፣ በኢሉአባቦራ፣ በከፋ እና በሸካ ዞኖች ላይ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የነበረዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከ5-30 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል በማሻና በቴፒ ከ1- 2 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተዉሏል (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነጻጸር በማሻ መደበኛ የሆነ የዝናብ መጠን የነበረ ከመሆኑ በስተቀር ሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅና ፀሐያማ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3) ፡፡

ካርታ 1 ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2019 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21-31/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት የጃንዋሪ የመጨረሻው አስራ አንድ ቀናት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለ እንደነበር የተተነተኑ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ በአንዳንድ ድህረ ሰብል ስብሰባ ባልተጠናቀቀባቸው የመኸር አብቃይ አካባቢዎች አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ቢሆንም፤ በአንዳንድ ለበልግ ወቅት የማሳ ዝግጅት ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች አሉታዊ ጎን ነበረው። ከደረቃማውና ከነፋሻማው የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ አንፃራዊ በሆነ መልኩ የመሻሻል ሁኔታ ቢታይበትም፤ በአንዳንድ ለውርጭ ተጋላጭ በሆኑት የሰሜን፣ የመካከለኛዉ የደቡብ እና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ይህም ሁኔታ በቋሚ ተክሎች እንዲሁም በመስኖ በመታገዝ ለሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎችና በጓሮ አትክልቶች ላይ በመጠኑም ቢሆን አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ከነበረዉ ደመና በጉጂ፣ በኢሉአባቦራ፣ ከፋ እና ሸካ ዞኖች ላይ የተስተዋለው አነስተኛ እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4) ።

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2019 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21-31/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21-31/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ በአብዛኛዎቹ የሀገራችን ተፋሰሶች ላይ ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ተስተዉሏል፡፡ ይህንን ተከትሎ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደራቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደነበር መረዳት ተችሏል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በደቡብና በምስራቅ ተፋሰሶች ላይ እንደነበረ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል ባለፉት አስር ቀናት አልፎ አልፎ በጥቂት ምስራቃዊ ባሮአኮቦና ኦሞጊቤ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እስከ መጠነኛ እርጥበት ነበራቸዉ (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2019 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1-10/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በፌብሪዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚስተዋለው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት በስተቀር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማው የአየር ሁኔታ ያመዝናል፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማው የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1-10/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በፌብሪዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በአብዛኛዎቹ አካባቢዎች ላይ ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ የሚያመዝን ቢሆንም፤ ጥቂት የአጭርና የረጅም ጊዜ ሰብል አምራች በሆኑ የደቡብና የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች መጠነኛ እርጥበት የሚያገኙበትና የማሳ ዝግጅት ማድረግ የሚጀምሩበት ጊዜ ነው፡፡

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥሉት የፌብሪዋሪ የመጀመሪያ አስር ቀናት በሁሉም የሀገሪቱ ክፈሎች ላይ ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ እንደሚያመዝን ይጠበቃል፡፡ ምንም እንኳን ደረቃማው የእርጥበት ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ የሰብል ስብሰባ ተግባራትን ላላጠናቀቁ አካባቢዎች በጎ ሚና ቢኖረውም፤ ለበልግ እርሻ የማሳ ዝግጅት ለማድረግ አስቀድመው ማከናወን ለሚጠበቅባቸው አካባቢዎች አሉታዊ ጎን የሚኖረው ሲሆን፤ በተጨማሪም የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ላይ ጫና ማሳደሩ ስለማይቀር የሚመለከታቸው አካላት ከወዲሁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1-10/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በሁሉም የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህንን ተከትሎ በበልግ ወቅት የሚኖረዉ የቀን ሙቀት የዉሃን ትነት በመጨመር በተፋሰሶች ላይ ተጽኖ ሊያሳድር ስለሚችል ዉሃን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡